IBO IB DIPLOMA PROGRAMME
PROGRAMME DU DIPLÔME DU BI
PROGRAMA DEL DIPLOMA DEL BI

M07/1/A1AMH/HP1/AMH/TZ0/XX

22070013

**AMHARIC A1 – HIGHER LEVEL – PAPER 1**
**AMHARIQUE A1 – NIVEAU SUPÉRIEUR – ÉPREUVE 1**
**AMHÁRICO A1 – NIVEL SUPERIOR – PRUEBA 1**

Monday 14 May 2007 (morning)
Lundi 14 mai 2007 (matin)
Lunes 14 de mayo de 2007 (mañana)

2 hours / 2 heures / 2 horas

---

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Write a commentary on one passage only.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- N'ouvrez pas cette épreuve avant d'y être autorisé(e).
- Rédigez un commentaire sur un seul des passages.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Escriba un comentario sobre un solo fragmento.



© IBO 2007

**ከሚከተሉት ምንባቦች አንዱን መርጠህ(መርጠሽ) አስተያየት ስጥ(ስጪ)።**

***1. (ሀ)***

## ባዶ እጅ?

ሰቀቀኝ፤ እኔስ ሰቀቀኝ
ከተሸረሸረ ገላ
ከተጋጠ ምድር ተልጦ
ወፍ ከራቀው ጎጆ
ከቸመቸም ዛፍም ተሸምጦ
ሲዘረጋ
ባዶ እጅ ሲዘረጋ
ማለፊያ ማያዬን ሲዘጋ
"አምጣ" ሲለኝ
ተዘረጋ
"አምጣ" አለኝ!

ሰቀቀኝ፤ እኔስ ሰቀቀኝ
ከማይታሰብ ጥጋጥግ
ከመካን ነፋስ ተወልዶ
ወዳፍንጫዬ ተሰዶ
ባዶ እጅ
"አምጣ" ሲለኝ
"ወንድምዬ፣ ራበኝ አምጣ
ልጁ አምጣ፣ ወገን አምጣ
ራበኝ፣ ሞትኩኝ
አምጣ፣ አምጣ!
አምጣ፣ አምጣ!

በሦናነቷ ተጨኌንቃ
ነፍሴ ከነፍሴ ተላቃ
ተፈልቅቃ
ጩረቃ ሽራፋ ዶቃ
ከነተበ ጥብቆዋ
ከድብቋ ተፈልቅቃ
አዱኛዋን በማሕፀኗ
ውበቷን ባፍረት ደብቃ
ፀሐይም ጥርሷን አግጣ
የከቸቸ ግሮሮዋን
ባሳር ኮርኩራ አምጣ
"አምጣ!
አምጣ ስጠኝ!
በማትፈልጋት ሳንቲም
እራት ዳቦዬን ጋግርልኝ።
አምጣ ራበኝ!
አምጣ ራበኝ!"
ሳር ቅጠሉ አለቀሰ፤
ሰማይ ምድሩ ተማጠነኝ!

ጨነቀኝ፤ እኔስ ጨነቀኝ
የቱ ሴይጣን፣ የቱ መልአክ
የመስጠትን ሽምቀቆ
ከማንቁርቴ አስገባብኝ?

ሰብእነቱን ለማመን
ቁራጭ መጠርጠር ባይገደኝ
"ስጠሁህ፣ ምስጋና ስጠኝ
እርካታ ስጠኝ" ቢመረኝ
ሰቀቀኝ፤ እኔስ ሰቀቀኝ!

ለምን ይሆን ይህ ባዶ እጅ
ይህ ራቁት እጅ-ማይለየኝ?
ብሸሸውም እማይርቀኝ
ብገፋውም እማይለቀኝ?

ፍርጃ ይሆን ውርጅብኝ?
ፍጥረት ይሆን አጣብቂኝ?
ማልለየው እማይተወኝ?

ምንድነኝ፣ እኮ ምንድነኝ?
መስጠት ነኝ ወይስ ስጦታ
የመሆን ወህኒ ፍርደኛ
የመሆን ዓለም ከርታታ?
ባዶ-ጅ ነኝ ችሮታ፤
መሞያና መሙያ ቦታ?
ወይስ...?

ሰቀቀኝ፤ አንተው ሰቀቀኝ
ንፍገት ከደግነት ቢሳከር
እሰጥ እቀበለው ቢጠፋኝ!

ስንቅነህ እሸቱ፣"ባዶ እጅ"፣ <u>40 ጠብታዎች</u> ፣አዲስ አበባ፣ **1996**።

**1. ለ**

# የፈቅይበሉ ደብዳቤ

መነሻ ሀሳብ
አንቷን ፓቪሎቭች ቼኾቭ

ቀኑ መሸትሸት ብሏል። ከተቀመጠበት የጓዳ ክፍል ሆኖ ቀለሟ የምታቋርጥ እስክርቢቶውን በእጆቹ መሃል አስገብቶ እያሻሸ አገር ቤት ላሉት ወንድ አያቱ ደብዳቤ ለመፃፍ በመጣደፍ ወዲያና ወዲህ በዐይኑ ያማትራል።

ፈቅይበሉ እንዳይላሉ ይባላል ። የአስራ አምስት ዓመት እድሜ ያለው መልከ መልካም ታዳጊ ወጣት ነው። እድሜው ካለው አካላዊ ጥንካሬ ጋር ሲነፃፀር በልጅነቱ ጀምሮ በሥራ ተፈትኖ ያደገ ለመሆኑ አያጠራጥርም ። አምና የጥቅምት ሚካኤል ዕለት ነው የሟች አባቱ ታላቅ እህት ከገጠር ወደ አዲስ አበባ ያመጡት። እናቱም በወሊድ ምክንያት ከአባቱ ሦስት ዓመት ቀደም ብለው ነው የሞቱት። በዚህ የተነሣ የአባቱ አባት ጋር ነበር የሚኖረው። በእርግጥ ተወልዶ ያደገባት የኤፍራታና ጅሌ የገምዛ ወረዳ የሳር አምባ ጊዮርጊስ የገጠር መንደር ለህይወቱ ልዩ ትርጉም ነበራት። ሆኖም ግን፣ አባቱን በርስት ጭቅጭቅ የተነሳ ባላንጣዎች ከገምዛ ቆላ የማሽላ ዝሪት ሲያካሂዱ ውለው አመሻሽ ላይ ቢሻኖ ወንዝ ዳርቻ ገድለዋቸው ወደ ላይ ወደ

ደጋው ከሸኙ ጀምሮ በልጅነቱ በሐዘንና በቁጭት ሲብከነከን፣ በየአረሁ ሲሸልልና ሲፎክር የተሰማራበትን የከብቶቹን፣ የበጎቹንና የፍየሎቹን ፣እንዲሁም የጋማከብቶቹን እረኝነት በአግባቡ ሳይወጣ በመቅረቱ አያቱን ከመንደሩ ነዋሪዎች ጋር እያጋጨ አስቸግሮ ነበር። በዚህም አዲስ አበባ ለሚገኙት የአባቱ ታላቅ እህት በአደራ ተሰጠ።

ደንገዝገዝ ባለው የቅዳሜው ምሽት የአክስቱ ባልና አክስቱ ከሄዱበት ሳይመለሱ ቶሎ ቶሎ ዕፎ በፖስታ ለማሸግ ተጣደፈ።

ቀለሟ በየቦታው የተቆራረጠችውን እስኪሪቢቶ በጣቶቹ መሀል አስገባና ለመፃፍ ከእስክሪቢቶዋ ጋር ወደ ወረቀቱ ጎንበስ አለ።

'በኤፍራታና ጅሌ በገምዛ ወረዳ በማጀቴ ከተማ ሣር አምባ ጊዮርጊስ ለሚገኙት ውድ አያቴ ቄስ አንዳርጌ ዳምጤ ለጤናዎ እንደምን አሉ።

አባበይ! ግራ ቀኙን ታሰላስል አገሬንና አንቱን፥ ውድማውንና ፍየሎቹን ፥ በጎቹንና አህዮቹን ፥ በሮቹንና ላሞቹን ትናፍቅ እምባዬ የዳመና ግርዶሽ ይሰራል።

ታገሬ የአባቴን ደም ታልከፍል መነቀሌን ታስታውስ ሁለትዜ አንደሞትኩ ቆጠርኩት። አንዱ የአባቱን ደም ተቀብቶ ታገሩ የሸሸ እያለ አገሬው ያብጠለጥለኝ ጊዜ፣ ደሞ ሌላው እየሀ ጥሩና ቆሻሻው ፥ ሰውና ገለባው ፥ ወንድና ሴቱ ያለየበት አገር አዲስ አባ ተቀምጬ የአክስቴ ሰካራም ባል

ጠጁን እየጋፈ ማታ ማታ በካልቾ ያጎነኝ ጊዜ ነው።

አባበይ! በአገርሁ ታቦት በሣር አምባ ጊዮርጊስ ፥ ጅረት እያቋረጥሁ ጥዋውን በጠጣሁት በሳስነት ገብርኤል፥ቆመሁ ቅኔ ከማዕልት በመሩበት በሰለሁላ ሚካኤል ይገፍዋታለሁ እጄን ይዘው ለአገሬ አብቁኝ ። አገሬ ገብቼ የአባቴን ደም ከፍዬ እንደ አገሬ ዝንጀሮ በገደል በኖርኩ። አበባይ ! ሁለተኛም እርስዎን አላስቸግር ... ሌላው ቀርቶ ተቀን ሁለትዜ እግርዎን ባጥብስ ... በየማበሩ ቤት ቀን ተሌት ሳልበሳጭ ብወስድዎትስ፣ ለመሆኑ ቅር ይለዋል ብለው ነው ? አድኑኝ አባበይ ! አባበይ አድኑኝ!...ኑሮ እንዳይመስልዎ። የአባቴን ደም ሳልወጣ እንዳልሞትብዎ! ደሞም ባረጁ ጊዜ ሁሉ እጦርዎታለሁ። ወደ ደጋው አማሻ ገበያ ቢልኩኝ ፥ በማጀቴ በኩል አድርጌ ጨፋ ሮቢት ጊደር ግዛ ቢሉኝ፥ የትም አገር ቢልኩኝ እምቢ አልልም ። አባብዬ...ብቻ ለአገሬ ያብቁኝ።

ቅዳሜ ቅዳሜ ማጀቴ ገበያ እንኳ በአቅሟ ሰው ተፈልጎ እንደማይገኝባት ያውቃሉ እንኳንስ አዲሳባ።

አባበይ! ባህር ያቃሉ? ባህር ነው አዲሳባ። ወዴት ጫፍ ብዬ በየት በኩል ብዬ የአገሬን መንገድ ልወቀው። አባበይ! ከትናንት ወዲያ ተደብድቤ ነው የዋልኩት። እንዴት መሰልዎ! ቀበሌ ተልኬ አስር ኪሎ ስኳር ገዝቼ ወደ ቤት ስመለስ ስኳሩን የያገዘኩበት መቋጠሪያ ተቀዶብኝ ስኳሩ መንገድ ላይ በመፍሰሱ ነው። መቋጠሪያው

ብርሃኑ አዳፍሬ:: «የፈቅ ይበሉ ደብዳቤ»: <u>የጥቁሮች ህልምና ሌሎች</u>: ንግድ ማተሚያ ቤት: 1980::